**Important Information About Required Vaccinations for 7th Grade Entry-Amharic**
**ለ7ኛ ክፍል መግቢያ ስለሚያስፈልጉ ክትባቶች ጠቃሚ መረጃ**

**በቨርጂኒያ ውስጥ በቨርጂኒያ ኮድ ክፍል [§ 22.1-271.2](#) መሰረት ሰባተኛ ክፍል ከመግባቱ በፊት በቨርጂኒያ ትምህርት ቤት ለሚማሩ ተማሪዎች ሁሉ የ Tdap ክትባት፣ የ MenACWY (ሜኒንጎኮካል) ክትባት እንዲሁም የ HPV ክትባት መከተብ ይኖርባቸዋል**

*የክትባት መረጃ:*

- **የ Tdap ክትባት** ከቴታነስ፣ ዲፍቴሪያና ፐርቱሲስ (ትክትክ ሳል) የሚከላከል ነው፡፡ እነዚህ ከባድ በሽታዎች ሲሆኑ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በለጋነታቸው በእነዚህ በሽታዎች ላይ ክትባቶችን በሚወስዱ ጊዜ እራሳቸውንና በአካባቢያቸው ያሉትን ሰዎች ለመጠበቅ "ማጠናከሪያ" ያስፈልጋቸዋል፡፡
- **የ MenACWY (ሜኒንጎኮካል) ክትባት** ከማጅራት ገትር በሽታ ጥበቃን የሚሰጥ ሲሆን ህመሙ ብዙም ያልተለመደ ነገር ግን ከባድና ለህልፈት የሚዳርግ ከባድ የሆነ የባክቴሪያ በሽታ ኢንፌክሽን የሚያስከትል ነው፡፡ በአሥራዎቹ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣቶችና አዋቂዎች ለዚህ ህመም የመጋለጥ እድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ወደ 12ኛ ክፍል ከመግባቱ በፊት የማጠናከሪያ መጠን (ዶስ) ያስፈልጋል፡፡
- **የ HPV ክትባት** ከሂውማን ፓፒሎማቫይረስ ኢንፌክሽን የሚከላከል ሲሆን ይህ ቫይረስ አብዛኛውን የማህጸን በር ካንሰርን ጨምሮ ስድስት አይነት ካንሰርን ያስከትላል፡፡

*Tdap እና MenACWY መስፈርቶች ዝርዝር:*

- የተማሪዎ Tdap እና MenACWY (ሜኒንጎኮካል) ክትባቶች (ወይም ከህክምና ወይም በሃይማኖት የተነሳ ነጻ ስለመሆኑ ማረጋገጫ) ሰባተኛ ክፍል ከመጀመሩ በፊት ለትምህርት ቤት ክሊኒክ ማቅረብ ይኖርብዎታል፡፡
- ከ 7 አመት በፊት የተሰጡ የ Tdap መጠኖችና ከ10 ከአመት በፊት እንደተሰጡ የ MenACWY መጠኖች እንደተሰጡ አይቆጠሩም
- **የ Tdap እና MenACWY በሰነድ የተደገፈ ማስረጃ ልጅዎ ለ 2023-2024 የትምህርት ዘመን በአካል ትምህርት ቤት ተገኝቶ እንዲማር ወይም በእንቅስቃሴዎች ላይ እንዲሳተፍ ወቅቱን የጠበቀ መሆን <u>አለበት</u>፡፡**
- 

*የ HPV መስፈርቶች ዝርዝሮች:*

- ሰባተኛ ክፍል እንዲገቡ ለሚደረጉ ተማሪዎች የተሟላ ባለ 2 መጠን ተከታታይ የ HPV ክትባት ያስፈልጋል፡፡
  - በጤና ቦርድ የጸደቁ የትምህርት መርጃዎች ላይ ግምገማ ካደረጉ በኋላ፣ ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣ በራሳቸው ውሳኔ፣ ተማሪቸው የ HPV ክትባት እንዳይወስድ የራሳቸውን ምርጫ ማድረግ ይችላሉ፡፡ **ወላጅ ተማሪቸው ይህንን ክትባት እንዳይወስድ የሚመርጡ ከሆነ ከዚህ ነጻ እንዲሆን የሚገልጽ የመልቀቂያ ቅጽ ወይም የጽሁፍ ሰነድ የሚያስፈልግ <u>አይሆንም</u>፡፡**
- ይህንን መረጃ ከስቴት ጤና ኮሚሽነር ስለ HPV ውጤታማነትና አስፈላጊነት የተላከ ደብዳቤን አካቶ እዚህ ማግኘት የሚችሉ ይሆናል: [የ HPV መረጃ ደብዳቤ](#)

*ልጄ ክትባቱን እንዲከተብ የት መውሰድ እችላለሁ?*

የ Tdap፣ MenACWY እና HPV ክትባቶችን ለመከተብ ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ የትኛው ለተማሪዎ የተሻለ እንደሆነ ለመወሰን የትምህርት ቤትዎን [የህዝብ ጤና ነርስ](#) ያነጋግሩ፡

- **ከተማሪዎ የመጀመሪያ ደረጃ ሕክምና ሰጪ**
  - እነዚህ አስፈላጊ የሆኑ ክትባቶች በመድህን ዋስትና እቅዶች ስር ሽፋን ያገኛሉ፡፡ ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ ጥድፊያን ለማስቀረት እንዲቻል አሁኑኑ ቀጠሮ ይያዙ! ይህ ለሙሉ የጤና ግምገማ መልካም አጋጣሚ ነው፡፡
- **በ 2100 Washington Blvd ከሚገኘው የአርሊንግተን ካውንቲ የክትባት ክሊኒክ**
  - Tdap፣ MenACWY (ማኒንጎኮካል) እና HPVን ጨምሮ የሚያስፈልጉ ክትባቶች ያለ ምንም ክፍያ የሚሰጡ ሲሆን ሌሎች የሚመከሩ ክትባቶች የሚያካትቱ ሊሆኑ ይችላሉ (ድረገጹን ይመልከቱ)
  - ቀጠሮ መያዝ የሚያስፈልግና የጥበቃ ጊዜውም ሊለያይ ይችላል፡፡ የስራ ቀናትና ሰአቶች እዚህ ይገኛሉ: [የክትባት ክሊኒክ - የአርሊንግተን ካውንቲ ኦፊሴላዊ ድረ-ገጽ (arlingtonva.us)](#)
- **ከየተማሪዎ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጤና ክሊኒክ**
  - የትምህርት ቤትዎ [የጤና ክሊኒክ](#) በዚህ የጸደይ ወቅት ለ Tdap፣ MenACWY እና HPV ክትባቶች ትምህርት ቤትን መሰረት ያደረገ የክትባት እድሎችን ያመቻቻል፡፡
  - እነዚህን ክትባቶች በትምህርት ቤት ክሊኒክ ለመቀበል ምንም አይነት ክፍያ የማይፈጸም ቢሆንም ነገር ግን ብቁነትና የመድህን ዋስትና እንደ የግዴታ የስምምነት ሂደት አካል ይታያሉ፡፡
  - በየትኛውም አይነት ምክንያት ክትባቱ በትምህርት ቤት መሰጠት የማይቻል ከሆነ ተማሪው ሁሉንም የትምህርት ቤት መግቢያ የክትባት መስፈርቶችን ማሟላቱን ማረጋገጥ የወላጅ/አሳዳጊ ሃላፊነት ነው፡፡

**የአሁኑን የቨርጂኒያ ደንብና ለተደጋጋሚ ጥያቄዎችን እነዛን ጨምሮ ተጨማሪ መረጃ በቨርጂኒያ የጤና መምሪያ ድረገጽ: [የትምህርት ቤት መስፈርቶች - ክትባት (virginia.gov)](#) ማግኘት ይችላሉ፡፡ ማንኛውም ጥያቄ የሚኖርዎ ከሆነ እባክዎን የትምህርት ቤቱን [የህዝብ ጤና ነርስ](#) ያግኙ፡፡**